የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ — የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 14
ADDIS ABABA – 15th February, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፳፮/፲፱፻፹፰ ዓ.ም.
የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅን ለመሻር የወጣ አዋጅ ........................................ ገጽ ፻፵
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፰ዓ.ም
የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .......... ገጽ ፻፵፩

## CONTENTS

Proclamation No. 26/1996
A Proclamation to Repeal the National Research Institute of Health Establishment Proclamation ............................................. Page 140
Council of Ministers Regulations No. 4/1996
The Ethiopian Health and Nutrition Research Institute Establishment Council of Ministers Regulations ................................................ Page 141

### አዋጅ ቁጥር ፳፮/፲፱፻፹፰
### የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅን ለመሻር የወጣ አዋጅ

የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትን አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፩/፲፱፻፸፯ መሻር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅን ለመሻር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፳፮/፲፱፻፹፰» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. መሻር

የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፩/፲፱፻፸፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፫. መብትና ግዴታ ስለማስተላለፍ

የብሔራዊ ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት መብትና ግዴታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፰ ለተቋቋመው የኢትዮጵያ የጤናና ሥነምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ተላልፏል ።

### PROCLAMATION NO. 26/1996
### A PROCLAMATION TO REPEAL THE NATIONAL RESEARCH INSTITUTE OF HEALTH ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it is found necessary to repeal the National Research Institute of Health Establishment Proclamation No. 271/1985;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "National Research Institute of Health Establishment Proclamation Repealing Proclamation No. 26/1996."

2. *Repeal*

The National Research Institute of Health Establishment Proclamation No. 271/1985 is hereby repealed.

3. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the National Research Institute of Health are hereby transferred to the Ethiopian Health and Nutrition Research Institute established under Council of Ministers Regulations No. 4/1996.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከየካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

4. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of the 15th day of February, 1996.

Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

---

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፰

## <u>የኢትዮጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትየጵያ የጤናና ሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬/ ፲፱፻፹፰ " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>መቋቋም</u>

፩· የኢትዮጵያ የጤናና የሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት (ከዚህ በኋላ "ኢንስቲትዩቱ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ ተቋም በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ኢንስቲትዩቱ ተጠሪነቱ ለጤና ጥበቃ ሚኒስትር ይሆናል ።

· <u>ዋናው መሥሪያ ቤት</u>

የኢንስቲትዩቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ሥፍራዎችም ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ለማቋቋም ይችላል ።

፬· <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፤

፩· የበሽታ መንስኤና ስርጭትን ፣ ሥነ ምግብን ፣ የህገረሰብ መድኃኒትና የሕክምና ዘዴዎችን እንዲሁም ዘመናዊ መድኃኒቶችን በተመለከተ ጥናትና ምርምር በማካሄድ በሀገሪቱ ጤናን ለማሻሻል የሚደረገውን እንቅስቃሴ የማገዝ ፤

፪· የጤና ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲዳብር አስተዋጽኦ የማድረግ።

፭· <u>የኢንስቲትዩቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· ለምርምርና ጥናት የሚረዱ መረጃዎችን የመሰብሰብ ፣ የማጠናቀር ፤

፪· ለጤና ምርመራ ፣ ለበሽታ መከላከያና ለሕክምና የሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮች ዝግጅትን በተመለከተ ጥናትና ምርምር የማድረግ ፤

፫· የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለማከናወን ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ወይም ተቋሞች ጋር ቅንጅታዊ አሠራር እንዲቀየስ ፣ እንዲጠናከርና እንዲዳብር የጋራ ምርምር እንዲፈጠር የመጣር ፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 4/1996

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN HEALTH AND NUTRITION RESEARCH INSTITUTE

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.4/1995.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Ethiopian Health and Nutrition Research Institute Establishment Council of Ministers Regulations No. 4/1996."

2. *Establishment*

1) There is hereby established the Ethiopian Health and Nutrition Research Institute (hereinafter "the Institute") as an autonomous public authority having its own legal personality.
2) The Institute shall be accountable to the Minister of Health.

3. *Head Office*

The Institute shall have its Head Office in Addis Ababa, and may establish branch offices elsewhere as may be necessary.

4. *Objectives of the Institute*

The Institute shall have the following objectives:

1) to conduct research on the causes and spread of diseases, nutrition, traditional medicines and medical practices and modern drugs and thereby support the activities for the improvement of health in the country.
2) to contribute to the development of health science and technology.

5. *Powers and Duties of the Institute*

The Institute shall have the following powers and duties:

1) to collect and compile data for research;
2) to conduct research on the production of diagnostic, prophylactic and therapeutic substances;
3) to make joint efforts with the concerned offices or institutes for the initiation of research activities;

፬· የምግብ እጥረትና ያለመመጣጠን የሚያስከትላቸው በሽታዎች የሚወገዱበትን መንገድና በቤተሰብ ደረጃ የአመጋገብ ሁኔታ እንዲሻሻል ጥናትና ምርምር የማድረግ፤

፭· የበሽታዎችን መንስዔ፣ የሚያስከትሉትን ጠንቅና ሥርጭት በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ጥናትና ምርምር የማካሄድ ፤

፮· በሀገረሰብ መድኃኒትና ህክምና እንዲሁም በዘመናዊ መድኃኒቶች ላይ ምርምር የማካሄድ ፤ አጥጋቢ የምርምር ውጤት ያሳዩ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው የሀገረሰብ መድኃኒቶችና የህክምና ዘዴዎች በጤና አገልግሎት ውስጥ የሚገቡበትን ሁኔታ የማጥናት ፤

፯· ከሌሎች አግባብ ካላቸው አካሎች ጋር በመተባበር በአገሪቱ ውስጥ የሥነ ምግብ ምርምርና ጥናት የማካሄድ ፤

፰· በላቦራቶሪና በክሊኒካል ጥናቶች ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድኃኒቶች ሊመረቱ የሚችሉበትን ሁኔታ የማጥናት ፤

፱· ፍቱን የሀገረሰብ መድኃኒቶችን አጠቃቀም ፣ ጥራትና ብቃት የሚገልጽ መነሻ መጽሐፈ መድኃኒት የማዘጋጀት፤

፲· የሀገረሰብ መድኃኒትና ሕክምና ባለሙያዎች ስለሙያው መጐልበትና ስለሚከተሉት የጤና አገልግሎት ጥራትና ብቃት ለመወያየት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣ ሥልጠናና ትምህርትም እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የመሥራት ፤

፲፩· በሀገረሰብ መድኃኒትነት የሚያገለግሉ ዕፅዋቶችና የሕክምና ቅርሶች እንዳይጠፉ የአካባቢ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ጥረት የማድረግ ፤

፲፪· እንደ አስፈላጊነቱ የሙያ ምክር የመስጠት ፤ እንዲሁም ከልዩ ልዩ ተቋሞች ለከፍተኛ ምርመራ ጥያቄዎች ሲቀርቡለት የሚላኩለትን ናሙናዎች በመቀበል የላቦራቶሪ ምርመራዎችን የማከናወን ፤

፲፫· ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ የማስከፈል ፤

፲፬· የንብረት ባለቤት የመሆን ፣ ውል የመዋዋል ፤

፲፭· በራሱ ስም የመክሰስ ፣ የመከሰስ፤

፲፮· ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን ።

፮· <u>የኢንስቲትዩቱ አቋም</u>

ኢንስቲትዩቱ ፤

፩· የዲሬክተሮች ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ) ፤

፪· በቦርዱ አቅራቢነት በመንግሥት የሚሾም አንድ ዲሬክተር፣

፫· አስፈላጊው ሠራተኞች

ይኖሩታል ።

፯· <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩· የጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር .................... ሰብሳቢ

፪· የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ተወካይ . አባል

፫· የሕክምና ትምህርት ከሚካሄድባቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች የሚወከሉ ባለሙያዎች ............ "

፬· በመንግሥት የሚሰየም አንድ አባል ........................ "

፭· የኢትዮጵያ የጤናና ሥነምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ዲሬክተር ......................................... አባልና ፀሐፊ

4) to undertake research on ways of preventing diseases due to malnutrition and nutritional deficiencies, as well as nutritional improvements at family level;

5) to undertake studies on the causes, health impacts and distribution of diseases, in collaboration with those concerned;

6) to do research on traditional and modern drugs as well as on traditional medical practices and study the integration of those found to be useful into the health service system;

7) to conduct nutritional science and technology research on food items in collaboration with other necessary bodies within the country;

8) to study the production of traditional drugs whose therapeutic efficacy and safety have been proven by laboratory and clinical researches;

9) to prepare a preliminary pharmacopoeia on traditional drugs;

10) to prepare, in collaboration with those concerned, conducive situations whereby traditional medicine practitioners can develop their profession through training and education to improve the quality of health services they render;

11) to cooperate with concerned organizations and put on all efforts for the conservation and protection of plants which serve as traditional drugs, and other medical antiques from extinction;

12) to impart professional consultancy services as deemed necessary, as well as receive and undertake laboratory tests on samples submitted at referral level;

13) to charge fees for the services it renders;

14) to own properties and enter itno contracts;

15) to sue and be sued in its own name;

16) to carry out such other activities as are necessary for the attainment of its objectives.

6. *Organization of the Institute*

The Institute shall have:

1) a Board of Directors (hereinafter "the Board");

2) a Director to be appointed by the Government upon the recommendation of the Board;

3) the necessary staff.

7. *Members of the Board*

| | |
|---|---|
| 1) The Vice Minister of Health ........ | Chairman |
| 2) a Representative of the Ethiopian Science and Technology Commission .............................................. | Member(s) |
| 3) Representatives of higher education institutions in the medical field ................................ | " |
| 4) a Member to be appointed by the Government ................................ | " |
| 5) The Director of the Ethiopian Health and Nutrition Research Institute .................................................... | Member & Secretary |

፰· <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩· በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ እና ፭ የተመለከቱት የኢንስቲትዩቱ ዓላማዎች እንዲሁም ስልጣንና ተግባሮች በሚገባ ሥራ ላይ መዋላቸውን የመከታተል ፤

፪· በኢንስቲትዩቱ ተቀርጸው የሚቀርቡትን ፖሊሲና መመሪያዎች የመገምገምና የማፅደቅ ፤

፫· የኢንስቲትዩቱን የምርምር ፕሮግራሞች ገምግሞ የማጽደቅ፣ በሥራ መተርጐማቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ፤

፬· ለኢንስቲትዩቱ ዲሬክተር ተጠሪ የሆኑ ኃላፊዎችን ሹመት የማጽደቅ ፤

፭· በቴክኒክና በሳይንቲፊክ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ሠራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ የማጽደቅ ፣ ደሞዝና አበላቸውን የመወሰን ፤

፮· የኢንስቲትዩቱን ረቂቅ በጀት የማጽደቅ ፣ አመዳደቡን የመመጠንና አወጣጡን የመወሰን ።

፱· <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

፩· ቦርዱ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል ። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል ።

፪· ከቦርዱ አባላት አብዛኞቹ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል ።

፫· የቦርዱ ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ። ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል ።

፬· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

፲· <u>የዲሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· ዲሬክተሩ የኢንስቲትዩቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ኢንስቲትዩቱን በሚገባ የማስተዳደርና ሥራውንም የመምራት ኃላፊነት አለበት ።

፪· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ዲሬክተሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ለኢንስቲትዩቱ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባሮች ሥራ ላይ የማዋል ፤

ለ) በኢንስቲትዩቱ በቴክኒክ እና በሳይንቲፊክ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሠራተኞችን ቦርዱ ባፀደቀው መመሪያ መሠረት የመቅጠር ፣ የማስተዳደር እንዲሁም የኢንስቲትዩቱን ሌሎች ሠራተኞች በመንግሥት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የማስተዳደር ፤

ሐ) የኢንስቲትዩቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ፤

መ) ለኢንስቲትዩቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ የማድረግ ፤

ሠ) የኢንስቲትዩቱን የሥራ ክንውን የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ለቦርዱ የማቅረብ ።

፫· የኢንስቲትዩቱን ተግባሮች በሚገባ ለማከናወን ባስፈለገ መጠን ሥልጣኑን በከፊል ለኢንስቲትዩቱ ምክትል ዲሬክተር ወይም ለሌሎች የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች በውክልና ሊሠጥ ይችላል ።

*8. Powers and Duties of the Board*

The Board shall have the following powers and duties:

1) to follow-up the implementation of the objectives as well as the powers and duties of the Institute provided in Articles 4 and 5 of these Regulations;
2) to analyze and approve policies and directives submitted by the Institute;
3) to evaluate, approve and monitor the research programmes of the Institute;
4) to approve the appointment of officials directly accountable to the Director of the Institute;
5) to approve the personnel regulations as well as fix the salary and allowances of the technical and scientific staff of the Institute;
6) to approve, as well as determine the allocation and disbursement of the draft budget of the Institute.

*9. Meetings of the Board*

1) The Board shall have its ordinary meetings every three months. Extraordinary meetings may be convened as deemed necessary.
2) There shall be a quorum where the majority of the members are present.
3) Decisions of the Board shall be passed by a majority vote. In case of a tie the Chairman shall have a casting vote.
4) Without prejudice to the provisions of this Article, the Board may issue its own rules of procedure.

*10. Powers and Duties of the Director*

1) The Director shall be the chief executive of the Institute and shall, subject to the general directives issued to him by the Board, be responsible for the proper management and direction of its activities.
2) Without limiting the generality of the provisions of sub-Article (1) of this Article, the Director shall:
   (a) exercise the powers and duties vested in the Institute under Article 5 of these Regulations;
   (b) employ and administer the technical and scientific staff in accordance with the personnel regulations approved by the Board as well as administer other personnel in accordance with federal civil service laws;
   (c) prepare the annual budget and work programme of the Institute and submit same to the Board;
   (d) effect payments in accordance with the approved budget and work programme of the Institute;
   (e) submit to the Board an annual report on the activities of the Institute.
3) The Director may delegate part of his powers to the Deputy Director or to other employees of the Institute to the extent necessary for the effective performance of the activities of the Institute.

## ፲፩· በጀት

፩· የኢንስቲትዩቱ በጀት ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፣

ሀ) ከፌዴራል መንግሥቱ የሚመደብ በጀት፣

ለ) በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰበሰብ የአገልግሎት ዋጋ፤

ሐ) ከሌሎች ምንጮች ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተመለከተው ገንዘብ በኢንስቲትዩቱ ስም ባንክ ተቀማጭ ሆኖ የኢንስቲትዩቱን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የመንግሥትን የበጀት አሠራር መመሪያ በማድረግ ወጪ ያደርጋል ።

## ፲፪· የሂሣብ መዛግብት

፩· ኢንስቲትዩቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል ።

፪· የኢንስቲትዩቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ ።

## ፲፫· ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

## *11. Budget*

1) The budget of the Institute shall be drawn from the following sources:
   (a) budgetary allocation by the Federal Government;
   (b) service fees collected in accordance with these Regulations;
   (c) any other source.
2) The fund indicated in sub-Article (1) of this Article shall be deposited in a bank in the name of the Institute and shall be expended, in accordance with Government budgetary rules, to give effect to the objectives of the Institute.

## *12. Books of Accounts.*

1) The Institute shall keep complete and accurate books of accounts.
2) The books of accounts and financial documents of the Institute shall be audited annually by the Auditor General or by other auditors designated by him.

## *13. Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 15th day of February, 1996.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE